SBS

# Media Release

5 October 2021




## SBS የወደፊቱን የSBS ራዲዮና ቋንቋ ግልጋሎቶች ለመቅረፅ የማኅበረሰብ ግብረ ምላሽን ይሻል

እያደጉ በመሔድ ላይ ያሉትን የወቅቱን የአውስትራሊያ ፍላጎቶች ማሟላት አንዱ የSBS የማያወላዳ ትግበራ ድርሻ ነው። SBS በ SBS ራዲዮ አማካይነት የሚሰጣቸውን የቋንቋ ግልጋሎቶች መደበኛ ክለሳ ጀምሯል። በዛሬው ዕለትም በረቂቅ የመረጣ መመዘኛዎቹ ላይ የግብረ ምላሽ ግብዣውን ለሕዝባዊ ምክክር ክፍት አድርጓል።

የSBS ቋንቋ ግልጋሎቶች ክለሳ የSBS ግልጋሎቶች በፍጥነት እየተለወጠና እየጨመረ ያለውን የአውስትራሊያ ሕብረተሰብ እንዲያንፀባርቅ ብሔራዊ የሕዝብ ቆጠራን ተከትሎ በየአምስት ዓመቱ የሚካሔድ ሂደት ነው። የመረጣ መመዘኛው እኒህ ግልጋሎቶቹ እንደምን ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ለማስረዳትና የትኛው ቋንቋ ግልጋሎት ማግኘት እንዳለበት የይሁንታ ውሳኔውን ከግብር ላይ የሚውለው የ2021 የሕዝብ ቆጠራ ዳታ ተመርኩዞ ነው።

የቋንቋ ግልጋሎቶቹ ክለሳ ራዲዮን ጨምሮ የSBS ኦዲዮና ቋንቋ የሚያበረክታቸውን SBS በጥያቄን፣ ፖድካስትና ሌሎች ዲጂታል መድረኮችን ያካትታል።

ከዛሬ ጀምሮ እስከ ኖቬምበር 12, 2012 ለስድስት ሳምንታት የሚቆየው ሕዝባዊ ምክክር ለማኅበረሰባት የSBS ሬዲዮ ግልጋሎቶችና አውታረ መረቡ የሚያበረክታቸውን ኦዲዮና ቋንቋን ጨምሮ ለመጨረሻ የመረጣ መመዘኛ መሥፈርቱ ከግምት ውስጥ እንዲያስገባቸው የሚያስችል ግብረ ምላሽ አስተዋፅዖ ጠቃሚ ዕድል ነው።

የ SBSየ ኦዲዮና ቋንቋ ይዘት ዳይሬክተር ዴቪድ ሁኣ "SBS የአውስትራሊያ ዝንቅ ማኅበረሰባት ዘንድ መድረሻ ልዩ ዘርፈ ብዙ የግንኙነት መድረክ ብቃት አለው። ከ45 ዓመታት በላይ ፈጠራና ትርጉም ባለው መንገድ ራሳችንን አዋድደን ዘልቀናል፤ ዛሬ በራዲዮ፣ ኦንላይን፣ ፖድካስት እና ኤፖች አማካይነት ከ60 በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ግልጋሎቶችን እያበረከትን እንገኛለን። ይህ ክለሳ 50ኛ ዓመቱ ላይ ለመድረስ እያመራ ላለው SBS ማነጫነት ያግዛል"

"የ SBS ዘርፈ ብዙ ቋንቋ ግልጋሎት ወሳኝ ሚና በኮቪድ -19 ወረርሽኝ ወቅት ሁነኛ ወቅታዊ መግለጫና የጤና መረጃን ለማኅበረሰባት በተመራጭ ቋንቋቸው በማቅረብ በግብር አስመስክሯል። የቋንቋ ግልጋሎቶች ክለሳ የዛሬይቱ አውስትራሊያን ፍላጎቶች በማንፀባረቅ እንዲቀጥል ለማስቻል ጠቃሚ ዕድል ነው።"

"በየጊዜው የቋንቋ አበርክቶዎቻችንን ማደሱ SBS የባሕላዊና ቋንቋዊ ዝንቅነት መደብ ጀርባ ላላቸው ትላልቅ ማኅበረሰባት የተሻለ ግልጋሎት እንዲሰጥ ያስችለዋል፤ እንዲሁም ቁጥራቸው በመጨምር ላይ ላሉትና በእጅጉ ግልጋሎት የሚያሻቸውን ማኅበረሰባት አክሎ። በዚህ ሂደት የአድማጮቻችን ድምፅ ወሳኝ አካል ነው፤ እናም በመላው አውስትራሊያ ማኅበረሰባት ግብረ ምላሻቸውን እንዲያጋሩን እናበረታታለን" ብለዋል።

የመረጣ መመዘኛው የመጠናቀቂያ ጊዜ ሜይ 2022 ነው። የተከለሰው የSBS ቋንቋ ግልጋሎቶች በ2022 መጨረሻ ግድም ግብር ላይ እንዲውል ይደረጋል።

የመረጣ መመዘኛው ሕዝባዊ የምክክር ጊዜ ከኦክቶበር 5 እስከ ኖቬምበር 12, 2021 ይዘልቃል። ረቂቅ የመረጣ መመዘኛውን ለመመልከትና ግብረ ምላሽዎን ለማስገባት sbs.com.au/consultation ይጎብኙ።

ፍጻሜ

ለተጨማሪ መረጃና ቃለ ምልልስ ጥያቄዎች እባክዎን Kate Warnock | kate.warnock@sbs.com.au | 0419 316 135 ያግኙ።